# ምዕራፍ ሶስት
# የስነ ጽሑፋዊ ሂስ ዓይነቶች

- **ስንት አይነት የስነጽሑፋዊ ሂስ አይነቶች አሉ?**
- **እስኪ የምታውቋቸውን ዘርዝሩ!**

ስነ ጽሑራዊ ሂስ ደራሲን፣ድርሰትንና አንባቢን መሰረት አድርጎ ሊካሄድ ይችላል ። ከድርሰት አንጻር ርዕሰ ጉዳይን ፣የአተራረክ ቴክኒክን፣የቋንቋ አጠቃቀምንና ቅርጽን መነሻ በማድረግ ሂስ ይሰጣል። ከደራሲ አንጻር ሲታይ ደግሞ የደራሲውን ሀሳብ፣እምነትና አመለካከትና የደራሲውን የህይወት ታሪክ መመርመር ይቻላል። ከአንባቢ አንጻር ሂስ ድርሰቱ አንባቢ ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ ይተነትናል።

### 1. *ሥነ-ምግባራዊ* ሂስ (Moralitisc Approch)

ስነ-ምግባራዊ ሂስ ከነፕሌቶ ጀምሮ በብዙ ሃያሲን ዘንድ በተግባር ላይ ይውል የነበረና የረጂም ዘመን ዕድሜ ያለው የሂስ አይነት ነው። ዋነኛ ትኩረቱም አንድ ሥነ-ጽሁፋዊ ስራ ይዞት በተነሳው ወይም ሊያስተላልፈው በፈለገው ቁም ነገር ላይ ነው። ስነ-ምግባራዊ ሂስ የሚያደርግ ሃያሲን የሚያስጨንቀው በስራው ምን ተባለ፣ ምን ቀረበ የሚለው ነው። እንዴት ቀርበ የሚለው ግን አያስጨንቀውም። በዚህ አይነቱ ሂስ የስነ-ጽሑፋዊ ስራዎች ድክመት ጥንካሬ የሚዳኘው ስራው *ከሚያንፀባርቀው የዘመኑ ስነ-ምግባር አንፃር ነው።* በዘመኑ በታወቁ ስነ-ምግባራዊ መርሆዎች በመሳሰሉት ስራው ምን ያህል ሰዋዊነት እንደሚንፀባረቅበት ይመዝናል። ስራው የዚያን ዘመን የስነ-ምግባር መርሆዎች ምን ያህል እንዳንፀባረቀ *ስነ-ምግባራዊ መርሆዎች መሰረት አድረጎ ለማህበረሰቡ የሚጠቅም ጉዳይ ማበርከቱና አለማበርከቱ ይመረምራል።* ሂሱም በዚህ ዙሪያ የሚያጠነጥን ይሆናል። አንድ አንባቢ ከፈጠራ ስራዎች ስለህይወት ምን ሊማር ይችላል? ከታሪኩ አንባቢው ምን ያክል መልካም ምግባራትን ያወርሳል? የሚሉትን ያጠናል። ባጠቃላይ የዚህ ሂስ ዋና አላማ የስነ ጽሑፍ ስራው ምን ያክል ስነምግባራዊ እሴቶችን እንደሚያንጸባርቅ መመርመር ነው። ሂሱ ቀዳሚ

የሂስ አይነት ቢሆንም ብዙ ነቀፍታዎች ገጥመውታል፡፡ ከነዚህ መካከል ከውበታዊነት ወይም ኪናዊነት ይልቅ ይዘት ላይ ብቻ ማተኮሩ የስነ ጽሑፍ ውበታዊ ፋይዳ እንዳይታ አድርጓል የሚለው አንዱ ነው፡፡

## 2. ፍካሬ ልቦናዊ ሂስ (psychoanalytic approach)

*ፍካሬ ልቦናዊ ሂስ የሚባለው ስነልቦናዊ ሂስ በሲግማንድ ፍሩይድ (1856-1939) የስነ ልቦና መርሆዎች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በስነ ልቦናውያን አረዳድ አለም የግለሰቦች ስብስብ ናት፡፡ እያንዳንዱ ግለሰብ ደግሞ ስነልቦናዊ ታሪክ አለው፡፡ ይህ ታሪኩ የሚጀምረው በህጻንነቱ ከቤተሰቡ ጋር ባለበት ጊዜ ሲሆን ጉርምስናው የልጅነት ልምዱ ላይ ይመሰረታል፡፡ በሰው ስብእና ውስጥ ከጨቅላነት እስከ ህጻንነት ከዚያም ሙሉ ሰውነት ድረስ አዕምሮ ሚመራባቸው ክፍሎች አሉ፡፡ እነሱም ኢድ፣ኢጎ እና ሱፐር ኢጎ በመባል ይታወቃሉ፡፡*

*ኢድ፡- በሌላ ነገር ተጽዕኖ ስር ሳንወድቅ የሚያስደስተንን ነገር ሁሉ እንዲናደርግ የሚገፋፋን የአዕምሮ ክፍል ነው፡፡*

*ኢጎ፡-ተከላካይ ክፍል ሲሆን በምክኒት በማመን ሁሉን በአግባቡ እንድናደርግ የሚያደርግ የአዕምሮ ክፍል ነው፡፡*

*ሱፐር ኢጎ፡- ይህ የአዕምሮ ክፍል የምናደርጋቸውን ተግባራት ሁሉ ከማህበረሰቡ ወግና ልማድ ጋር አስማምተን ሳናፈነግጥ እንድንኖርና እድንተገበር የሚያዘን ነው፡፡*

*በፍሮይድ አተያይ ማንኛውም የሰው ልጅ ባህሪና ድርጊት ከፍትወት ጋር ይያያዛል፡፡ ተምሰአሌቶችንና ትዕምርቶችን ጭምር በዚሁ እይታ ይፈታል፡፡ ማንኛውንም የኮንኬብ ቅርጽ ያለው ምልክት ሁሉ ከሴት ልጅ ብልት ጋርና ከሴትነት ጋር ሲያያዝ፣ (ኩሬዎች ፣አበባዎች፣ሲኒዎች፣ሰሀኖች፣የቡናፍሬ፣ዋሻዎች) የወንድ ብልት ቅርጽ ያላቸውን ትዕምርቶችና ምልክቶች ደግሞ ከወንድ ብልት ጋር ያመሳስላል፡፡*

ፍሮይድ ስነጽሁፍ የቁም ቅዠት (Day dream ) ነው ብሎ ያምናል፡፡ ይህ የቁም ቅዠት መነሻ የህጻንነት ፍላጎት ሲሆን በህፃንነት የተጨቆነ ፍላጎት (Repressed Sexual Motive) ነው፡፡ አንድ ህጻን ከጨቅላነቱ ጀምሮ የወሲብ ፍላጎት (ስሜት) አለው፡፡ ይህን ስሜቱን የሚያረካባቸው መንገዶች ደግሞ የተለያዩ ናቸው፡፡ ይህ ፍላጎት በህጻንነት እድሜው በአግባቡ ካልተስተናገደ በኢ.ንቁ ልቦና ውስጥ ይቆያል፡፡ ታዳ እነዚህ የልጅነት የፍትወት ተአቅቦ ውጤቶች ነፍስ ካወቁ በኋላ የሚወጡባቸው መንገዶች አሉ፡፡ እነሱም፡-

ቀልዶች ፣ጫወታዎች፣ህልሞች፣ ማስቲካ ማኘክ፣ ከንፈር መንከስ፣ ጣት መመትመት፣ብዙ መብላትና ዘማዊ ባህሪ ወዘተ ናቸው፡፡

በፍሮይድ አስተሳሰብ መሰረት ስነ ጽሑፍ የደራሲው ያልተሳኩ ፍትወታዊ ፍላጎቶች ወይም ዝንባሌዎች ገፍተው የሚወጡበትና የደራሲውን ውስጣዊ ነውጥ የሚያሳይ ጥበብ ነው፡፡ በደራሲው ኢ ነቁ አዕምሮ አድፍጠው የቆዩ ፍላጎቶች ስነ ጽሑፍን ሰበብ አድርገው ወጥተው ይታያሉ፡፡

ይህ አይነቱ የሂስ አይነት የደራሲውንም ሆነ የገፀ-ባህሪያቱን የውስጣዊ ህይወት መሰረቶች ፈልጎ፣ በማግኘት ላይ ያተኩራል፡፡ የዚህ የሂስ አይነት አራማጆች እንደሚያምኑት በአንድ ስነ-ጽሁፋዊ ደራሲና በድርሰት ስራው መካከል የጠበቀ ስነ-ልቦናዊ ቁርኝት አለ፡፡ የሂስ አይነቱም በደራሲውና በስነ-ጽሁፋዊ ስራው ገፀ-ባህሪያት የሰብዕና መልኮች ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ ስለሆነም የአንድን ደራሲ ስራ ለመተንተን ብሎም በውል ለመረዳት የደራሲውን የህይወት ታሪክ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ የደራሲውን ቤተሰብ፣ አስተዳደግ፣ የሚቀርባቸውን ሰዎች ማንነት አጠቃላይ አኗኗር በማወቅና ከስራው ጋር በማገናዘብ ስለደራሲውም ሆነ ገፀ-ባህሪያቱ መረዳት ይቻላል የሚል መነሻ ያለው ነው፡፡

በዚህ የሂስ አይነት ለአንድ የተወሰነ ስነ-ጽሁፍ ስራ መሰረት ደራሲውን የሚቀሰቅሰው አንዳች ስነ-ልቦናዊ ሁኔታ እንዳለ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ዋነኛ ትኩረቱ ይህን ስነ-ልቦናዊ ሁኔታ ለይቶ ማሳየት ነው፡፡ በመሆኑም በደራሲው በህይወት ዘመኑ የገጠሙት፣ የተመኛቸው፣ ያሳሰቡት ነገሮች በገፀ-ባህሪያቱ አማካይነት መንፀባረቅ አለመንፀባረቃቸውን ይመረምራል፡፡ ከደራሲው ህይወት ጋር ተመሳሳይነትም ሆነ ግንኙነት ማሳየቱ የዚህ ሂስ አንዱ ባህሪ ነው፡፡ በመሆኑም የዚህ ሂስ አንዱ ትኩረት ገፀ-ባህሪያት የሚፈጠርባቸውን ግጭቶች ከስራው ፈልጎ ማውጣትና የሚያስከትልባቸውንም ስነልቦናዊ ችግር መተንተን ነው፡፡

### 3. ማህበረሰባዊ ሂስ

ይህ የሂስ አይነት በማህበረሰብና በኪነ-ጥበብ መካከል ግንኙነት መኖሩንና ያንንም ግንኙነት መመርመር የኪነ ጥበባዊያን ስራ ለማጣጣምም ሆነ ለመረዳት አስፈላጊ ነው ብሎ የሚያምን ነው፡፡ በዚህ የሂስ አይነት ደራሲው የማህበረሰቡን ገፅታዎች ያን ያህል አንፀባርቋል የሚለው ቀዳሚ

ተግባር ነው። የስነ-ጽሁዋ ስራው *ጥንካሬም ሆነ ድክመት የሚመዘነው የማህበረሰቡን ፈርጀ ብዙ ህይወት በማሳየት ደረጃው* ይሆናል። ይህን ለማድረግ ደግሞ ሃያሲው የማህበረሰቡን ልዩ ልዩ ገፅታዎችን መረዳት ይጠበቅበታል። ሃያሲው የደራሲውን ስራ በሚገባ ለመተንተንና ሚዛናዊ ፍርድ ለመስጠት ድርሰቱ የተፃፈበትን ማህበረሰብ የነበረበትን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታ መገንዘብ (ማወቅ) ይኖርበታል። ከዚህም ሌላ *የዘመኑን ስነጥበባዊ ፍልስፍናዎች ወይም የስነ-ጽሁፍ ፈለጎች ማወቅ ስነ-ጽሁዋ ስራውን ለመረዳት ወሳኝ* ነው።

በአጠቃላይ ማህበረሰባዊ ሂስ ለማድረግ ቴክስቱን በተፃፈበት ዘመን ስለነበረው ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ፣ በዘመኑ ስለነበረው የማህበረሰቡ ባህልና አኗኗር እንዲሁም ዕውቀትና ስልጣኔ ግንዛቤ ሊኖረው ይገባል። እነዚህን ሁኔታዎች አስቀድሞ ከተረዳ በስነ-ጽሑፋዊ ስራው ላይ ከማህበረሰባዊ ሂስ አንፃር ተገቢ ሂስ ለመስጠት አያዳግተውም። ከዚህም በተጨማሪ *የዘመኑን ስነ-ጽሑፋዊ ፈለግ አስቀድሞ ካወቀ* ሂሱን በተገቢ መንገድ ለመስጠት ያስችለዋል።

## 4. ቅርፃዊ ሂስ (Formalism Criticism)

ቅርፃዊ ሂስ በ1920ዎቹና 1930ዎቹ አካባቢ ያቆጠቆጠ የሂስ አይነት ነው። የዚህ ሂስ አራማጆች ዋነኛ ትኩረትም ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች በራሳቸው ምሉዕ እንደሆኑና ሌሎች ውጫዊ ጉዳዮችን (የተፃፈበት ዘመን፣ የዘመኑ ፍልስፍና፣ ስነ-ጽሁፋዊ ፈለግ፣ የደራሲው ህይወት፣…) ማጣቀስና በእነሱ ላይ በመመርኮዝ ስነ-ጽሁፋዊ ስራን መመዘን ተገቢ እንዳልሆነ ማሳየት ነው። በመሆኑም በዚህ የሂስ አይነት *ከስራው ውጭ ባለጉዳዮች ስራውን ከመመዘን በጽሁፋዊ ስራው ላይ ብቻ ማተኮር ተገቢ ነው* የሚል እምነት አለው። ምክንያቱም ስነ-ጽሑፋዊ ስራ በራሱ ቅርጽ የሚኖርና የተወሰነ የውበት ደረጃ ብሎም የራሱ አወቃቀር ያለው ነው ከሚል እምነት የመነጨ ነው። በመሆኑም የትኛውም ስነ-ጽሑፋዊ ስራ ድክመት ጥንካሬው ሊለካ የሚገባው በራሱ *አፈጣጠራዊ ባህሪና አወቃቀር* መሆን እንዳለበት የሚያምን የሂስ አይነት ነው። ቅርጻዊ ሂስ ሁለትዋና ዋና የማይቀበሏቸው የስነ ጽሁፍ አተያች አሉ።

- ደራሲው ያሰበው ብሎ ስነ ጽሑፍን መሄስ (Intentional Fallacy)፡- ደራሲው ሊያስተላልፍ የፈለገው በራሱ በድርሰቱ ውስጥ ያለውን እንጅ እንደገና ደራሲውን በማሰብ የሚመጡ በቴክስቱ

ላይ የሌሉ ውጫዊ ሀሳቦች አይቀበሉም። ደራሲው ያሰበውም ይሁን የፈለገው ቴክስቱን ብቻ ነው በማለት ቴክስቱን ከተጽዕኖ ነጻ ያደርጋሉ።

- በአንባቢ ተጽዕኖ ስር ይወድቃል ማለት (Affective fallacy)፡- የድርሰት ስራው ትርጓሜ በተደራሲያን ስሜት፣ እምነትና አመለካከት ተጽዕኖ ደርስበታል የሚል አስተያየት አይቀበሉም። ደራሲና አንባቢን በመርሳት ተኩረትን ሙሉ በሙሉ በቴክስቱ ላይ ብቻ በማድረግ ሂስ መደረግ እንዳለበት ያምናሉ።

በአጠቃለይ ቅርጻዊ ሂስ በሚከተሉት መርሆዎች ለይ ይመሰረታል።

- ✓ ስነ ጽሑፍ ከደራሲው አላማና ምኞት ውጭ ትርጉም አለው።
- ✓ የደራሲው፣ የህይወት ታሪክ ማህበራዊና ታሪካዊ አውዶች ቦታ የላቸውም።
- ✓ ስነ ጽሑፍን ለመረዳት የሚስፈልጉን ነገሮች በሙሉ የሚገኙት በቴክስት ውስጥ ብቻ ነው።

በዚህ አይነቱ ሂስ ትኩረት የሚደረገው በድርሰት ውስጥ የተከሰተ ውበት፣ ውበቱ እንዴት ሊከሰት እንደቻለ? ያን ውበት እንዲከሰት ስላደረጉ የድርሰቱ ክፍሎችና ቅንጅታቸው፣… በመመርመር ላይ ነው። ለምሳሌ አንድ ረጅም ልቦለድ ላይ በዚህ የሂስ አይነት ሂስ የሚሰጥ ሃያሲ በታሪኩ አገነባብ በሚፈፀሙ ድርጊቶች ቅደም ተከተሎች፣ በአጠቃላይ በአተራረክ ጥበቡ ላይ፣ በአፃፃፍ ስልቱ፣ በቃላት ምርጫው ወዘተ. ሊያተኩር ይገባል። ይኸውም የረጅም ልቦለድን ግለወጥ ባህሪያትን መሰረት በማድረግ የሂ ስራውን ሊሰራ ይችላል።

## 5. *ሥረ መሰረታዊ ሂስ* (Basic Criticism)

በስረ መሰረታዊ ሂስ አንድ ስነ-ጽሑፋዊ ስራ ከተፃፈበት ዘመንና ከማህበረሰቡ ጋር ተያይዞ ድክመት ጥንካሬው የሚመዘን አይደለም። ከዚህ ይልቅ ስነ-ጽሑፋዊ ስራው ባንድ ወቅት ከተከሰተ የሰው ልጅ ታሪክ የተቀዳ ነው የሚል አቋም አለው። በመሆኑም ስለ መሰረታዊ *ሂስ ከባህል፣ ከዕምነትና ከሃይማኖት ጋር በተያያዙ ነገሮች ላይ የሚያተኩርና ያንንም አውጥቶ ለማሳየት የሚጥር* ነው።

በዚህ አይነቱ ሂስ ሃያሲው አንድን ስነ-ጽሁፋዊ ስራ ሲመለከት ሀተታ ተፈጥሯዊ ምንጮችንና ሃይማታዊ መሰረቱን ይመርጣል። ጥንታዊ ሰው ሲፈፅማቸው የነበሩ ባህላዊ ሀሳቦችን ከስነ-ጽሁፋዊ

ስራው ለይቶ በማውጣት ይተነትናል። በስነ-ጽሁፋዊ ስራው የቀረቡ ቀድሞ ይፈፀማቸው የነበሩ ነገሮችን (ፍቅር፣ ልደት፣ ሞት…) ስረ መሰረት በመፈለግ ላይ ያተኩራል።

## 6. አንባቢ ምላሽ ሂስ

ይህ የስነ-ጽሁፋዊ ሂስ በቅርብ ጊዜ የተስፋፋ የሂስ አይነት ነው። ይህ የሂስ አይነት እያንዳንዱ ስነ-ጽሁፋዊ ስራ ለእያንዳንዱ አንባቢ የሚሰጠው ትርጉም የተለያየ እንደሆነ የሚያምን ነው። የአንድ አሀድ (Text) ትርጉም የራሱ የአሀዱ ብቻ ሳይሆን የአንባቢውና የአሀዱ ጥምር ውጤት እንደሆነ የዚህ ሂስ አራማጆች ያስረዳሉ።
ዘሪሁን (1992) አንባቢ ምላሽ ሂስ የተለያዩ አንባቢያን አንድን ስነ-ጽሁፋዊ ስራ በእኩል ደረጃና ሁኔታ እንደማይገነዘቡት ብሎም አንድ አይነት ትርጓሜ እንደማይሰጡት ይገልፀዋል። ሰዎች ካላቸው የዕድሜ፣ የሚከተሉት እምነት፣ ባላቸው ባህላዊና ማህበራዊ እሴቶች፣ ወዘተ. መለያየት የተነሳ

አንድን ስነ-ጽሁፋዊ ስራ የማንበብና የመተርጎም አኳኋን እንዴት እንደሚለያይ ይመረምራል። ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች የራሳቸው የሆነ ክፍተት አላቸው። እነዚህ ክፍተቶች ደግሞ በንባብ ወቅት በአንባቢ መሞላት አለባቸው። ካለበለዚያ አሀዱ ሙሉ ትርጉም አይኖረውም። የስነ-ጽሑፋዊ ስራው ትርጉም የሚመጣውም አንባቢው በጽሑፍ ውስጥ ከተባሉት በመነሳት ያልተባሉ ነገሮችን ሲሞሉ እንደሆነም የዚህ የሂ አይነት መነሻ ነው። የአንድ ስነ-ጽሑፍ ስራ ሙሉ የሚሆነው አንባቢው አንብቦ ከራሱ ልምድ፣ ፆታ፣ ገጠመኝ፣ ዕውቀት፣ ዕድሜ፣ ወዘተ. አንፃር መሞላት ሲቻል ነው። ስነ-ጽሑፋዊ ሂስ የሚሰጠውም ስነ-ጽሑፋዊ ስራውን ከተለያዩ አንባቢያን እይታ አንፃር ምን ትርጉም ሊኖረው እንደሚቻል በማሳየት ነው።

## 7. አንስታይ ሂስ

ይህ የሂስ አይነት በ1960ዎቹ (እ.ኤ.አ) መጨረሻ አካባቢ የተጀመረና ከሴቶች ጉዳይ ጋር የሚያያዝ የሂስ አይነት ነው። የዚህ ሂስ አራማጆች እንደሚሉት የስነ-ጽሑፍ ቋንቋ የወንዶች የበላይነት የገነነበት ባህላችንን የሚያንፀባርቅ ነው ይላሉ። ዋና ትኩረቱም *በስነ-ጽሑፋዊ ስራዎች ውስጥ ሴት ገፀ-*

*ባህሪያት እንዴት ተስለዋል* በሚለው ላይ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ወንዶች በሴቶች ላይ የሚያደርሱትን ተፅዕኖ፣ ማህበረሰቡና የሚኖሩበት ባህል በሴቶች ላይ ያላቸውን *አመለካከትና የሚያደርስባቸውን ተፅዕኖዎች* ይመረምራል። የአንስታይ ሂስ ዋና አላማም ሴቶች በስነ-ጽሁፍ ውስጥ ያላቸው ሚና ከፍ እንዲልና ተሳትፏቸው እየጎላ እንዲሄድ ማድረግ ነው።

በአጠቃላይ የዚህ ሂስ አራማጆች እንደሚሉት በቀደሙት ስነ-ጽዠሑፋዊ ስራዎች ሴት ገፀ-ባህሪያት የወንዶች ጥገኞችና የፍትዎት መሳሪያ ብቻ ተደርገው ይሳላሉ። ብልህና ጀግና ሴት ስትሳል አልተስተዋለም። ስለዚህ ሴት ገፀ-ባህሪያት በስነ-ጽሑፋዊ ስራዎች ውስጥ እንዴት ተሳሉ፣ የሴቶች ጉዳይ እንዴት ተነሳ፣ ሴት ፀሀፍት ከወንዶች ፀሀፍት ይልቅ ሴቶችን እንዴት ሳሉ፣ ወዘተ. አይነት ጉዳዮች በዚህ የሂስ አይነት ይመረመራሉ። በዚያውም ፀሀፍት አውቀውም ሆነ ሳያውቁ የሚፈፅሟቸውን አድሏዊነት እንዲቀረፉ ለማድረግ ጥረት የሚደረግበት የሂስ አይነት ነው።

## 8. ህይወት ታሪካዊ ሂስ

ህይወት ታሪካዊ ሂስ ስነ-ጽሁፋዊ ስራን ከደራሲው የህይወት ታሪክ ጋር በማገናዘብ ትንተና የሚሰጥ ነው። በአንድ ስነ-ጽሁፋዊ ስራ ውስጥ ይብዛም ይነስም የደራሲው የህይወት ገጽታ፣ ፍልስፍና፣ ዝንባሌ ወዘተ. ይንፀባረቃል። ስለዚህ የደራሲውን ህይወት ማወቅ አንባቢያን ስራውን ይበልጥ ለመገንዘብ እንዲችሉ ይረዳል ከሚል እምነት የሚመነጪ የሂ አይነት ነው። አራማጆቹም የሚሉት አንባቢያን የአንድን ደራሲ የህይወት ታሪክ አውቀው ከስነ-ጽሁፋዊ ስራው ጋር እያገናዘቡ ማንበብ፣ ማጥናት፣ ወይም መመርመር ቢችሉ ለስነ-ፅሁፋዊ ስራው የሚኖቸውን ምላሽ ጥልቅ ያደርገዋል። ሃያሲው የደራሲውን የህይወት ታሪክ ካወቀ ከዚያ በመነሳት ጽሁፉ ስለተፃፈበት ዘመን፣ ስለዘመኑ ማህበረሰብ አኗኗር፣ ወዘተ. ትንተናውን ሊያካሂድ ይችላል። ይሁን እንጅ ይህ የሂስ አይነት በ20ኛው ክፍለ ዘመን በአድስ ሂስ አራማጆች (New Critics) ተቃውሞ ገትሞታል። በስነጽሁፍ ስራው የቀረቡ ታሪኮችና ሀሳቦች በሙሉ የደራሲው የራሱ ታሪካዊ ገጠመኞችና የህሕወቱ አካል አድርጎ መውሰዱ ስህተት እንደሆነ ተጠቁሟል።

## 9. ዘውጋዊ ሂስ (genric approach)

በዚህ ስነ-ጽሁፋዊ ሂስ ስነ-ጽሁፋዊ ስራን ከዘርፉ ባህሪ ጋር በማያያዝ የመመርመር ስልት። ይህ የሂስ ዓይነት ስነ-ጽሁፋዊ ስራው ረጅም ልቦለድ ከሆነ ከረጅም ልቦለድ ባህሪ አንፃር ብቻ ሊጠና ይገባል፤ ሌላውም ከራሱ ባህሪ አንፃር ብቻ ሊመረመር ይገባል የሚል መነሻ ያለው ነው። ይሁን እንጅ ይህ የሂስ አይነት ከሌሎቹ ስነ-ጽሁፋዊ ሂሶች የተነጠለ (ለብቻው) የቆመ እንዳልሆ ባለሙያዎች ይገልፃሉ።

በአጠቃላይ የሂስ አይነቶች እነዚህ ብቻ ናቸው ማለት አይደለም። ቀደም ባሉት ዘመናትም ሆነ አሁን በርካታ የሂስ አይነቶች ታይተዋል፣ እየታዩም ነው። ከላይ ከተጠቀሱት የሂስ አይነቶች በተጨማሪ ቅኝ ግዛታዊ ሂስ፣ ማርክሳዊ ሂስ፣ መዋቅራዊ ሂስ፣ ድህረ መዋቅራዊ ሂስ፣ አንድምታዊ ሂስ፣ ወዘተ. የተሰኙ የሂስ አይነታቸውም እንዳሉ ልብ ሊባል ይገባል። ከዚህ ባለፈም የሂስ አይነቶች የስነ-ጽሁፍ አተያይና ፍልስፍና በተለወጠ ቁጥር በየዘመኑ የሚከሰት በመሆን ወደፊትም የሚቆም አይደለም።